# እውነት መንፈሳዊ ጋዜጣ



በቦስተን የምትገኘው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ የምታምን የክርስቶስ ኢየሱስን የማዳን ወንጌል ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ የምታሰራጭ ቤ/ክ ነች። ይህም ጋዜጣ ወንጌልን ከምታሰራጭባቸው መንገዶች አንዱ ሲሆን በቤ/ክ የሥነ-ጽሁፍ አገልግሎት አባላት እየተዘጋጀ በየሁለት ወር አንድ ጊዜ ይቀርባል።

የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢ
ፖስተር ምሕረቱ ሌጂቦ
Email Meheretu2614@Yahoo.com
Telephone 617-792-5764

**ዋና አዘጋጅ.................. ሄኖክ ተሾመ**
**ምክትልአዘጋጅ........ ሐብታሙ አስረስ**
**የውብዳር ፍሰሐ**
**ኮምፒዩተርዝግጅት.....ትርሲት ጥላሁን**
**የፊት ገጽ ዲዛይነር.......ዝግጂት ክፍሉ**

ለቀጣዩ እትም ይረዳ ዘንድ የእናንተ ተሳትፎ ወሳኝ ሚና ስላለው በሚቀጥለው አድራሻ ያላችሁን አስተያየትና ጥያቄ ላኩልን።

***አድራሻችን***
***ለስነ-ጽሑፍ ክፍል***
Ethiopian Evangelical Church in Boston
88 Tremont Street
Boston, MA 02108
Email henokekka@yahoo.com
Tel 617 816 8827

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን በቦስተን
ETHIOPIAN EVANGELICAL CHURCH BOSTON
88 TREMONT STREET, BOSTON, MA, 02108
T: 617-523-5058 F: 617-523-5058
www.eecBoston.org

## ርዕሰ አንቀጽ

### እንድናገለግለው ተጠርተናል፤

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በአምሣሉ ሲፈጠር ዋና አላማ እንዲያገለግለው ነበር።ነገር ግን ሰው የተፈጠረበትን ዓላማ ዘንግቶ የሰይጣንን ሃሳብ በማስተናገዱ ከእግዚአብሔር ፈቃድና ሃሳብ ጋር ተጋጨ በዚህም ምክንያት ለሰይጣን እና ለራሱ ምኞት በመገዛቱ በክብር ፈንታ ውርደት በበረከት ፈንታ መርገም በህይወት ፈንታ ሞት በእረፍት ሰላም ፈንታ ጭንቀትና ሁከት በሰው ሁሉ ላይ ሆነ። የተሰጠውን መልካም እድል አጣ።

የእስራኤልን ሕዝብ እግዚአብሔር ከግብጽ ምድር ከፈርኦን እጅ ነፃ ባወጣቸው ጊዜ ያገለግለኝ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ ነው ያለው “ ለሕዝቡም የተናገረው ይህንኑ ነው ከግብጽ ባርነት ነፃ አወጣችኋለው በምድረ በዳ ታገለግሉኛላችሁ በማለት ያለውን ዓላማ ለሕዝቡ ገለጠ ነገር ግን የእሥራኤል ሕዝብ ባምላኩ ላይ አመጸ ከቃሉ እንዲህ ይላል “ቀኖቻቸው በከንቱ አለቁ ዓመቶቻቸውም በችኮላ “ የተሰጣቸውን እድል ሳይጠቀሙ በፈንታው በእግዚአብሔር ላይ አመጹ።

እኛስ በበጉ ደም የተዋጀን ከሞት ወደ ህይወት የተሻገርን ቀንበር የተሰበረልን ከሰይጣን እሥራት ነፃ የወጣን እርሱን ለማገልገል ፋቃዱን ለመፈጸም የተጠራንበትን ጥሪ አክብረን እድላችንን እየተጠቀምን ይሆን? እርሱን ለማገልገል የተጠራሁት ጥሪ አክብሬ እግዚአብሔር በሰጠኝ ፀጋ በመንግሥቱ ሥራ ውስጥ ተሰማርተው ከሚያገለግሉት አንዱ ነኝ ወይ? ብለን ራሳችንን ቆም ብለን እናያለን? ጌታ ኢየሱስ ለዚህ ምሳሌያችን ነው ፈለጉን ብንከተል እርሱ የመጣበትንና የኖረበት ዓላማ እግዚአብሔርን በማገልገል የሰውን ልጅ ማዳን ነው፤ ጌታ ራሱ እንዲህ ብሏል “የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም”” እንግዲህ ትርጉም ያለው ኑሮ እንኑር በዚች በምትጠፋና በምታልፍ ምድር የዋጀንንና ያዳነን ነፍሱን በመስጠት የራሱ ያደረገንን ጌታ ሃሳቡን አገልግለን የማናልፍ ከሆነ ምስኪኖች ነን ጌታን ባለማገልገል ያላለፍንበት ዘመን ያብቃና በዘመናችን ጌታን አገልግለን እንለፍ ጌታን ማገልገል ከመዳናችን ጋር የተሰጠን ጥሪ ነውና እርሱን በማገልገል ወደሚገኝ እርካታና እረፍት እንድንገባ ልዝቡን ቀንበር ቀሊሉን ሸክም በመሸከም ቀሪውን ዘመን እንዋጀው።

የቤተክርስቲያኒቷ:መልዕክት!

*ይህ አምድ የሰዎችን የሕይወት ምስክርነት የምናቀርብበት ሲሆን ለእግዚአብሔር ክብር ለሕዝቡም ጥቅም ይሆናል የምትሉት የሕይወት ምስክርነት ያላችሁ ወገኖች ደውሉልን ወይም ፊትለፊት አግኙን እናስተናግደለን*

# *ምስክርነት*

## *አሸንፌ ብሃለሁ፤*

*………………ካለፈው የቀጠለ*

*ባለፈው እትም እህት መቅደስ እናቷ አስጠር ተዋት ከክፍሏ ውስጥ የምትፈልገውን ነገር ካለ እንድ ታወጣ ሲጠይቋት እርሷም ለምን?ብላ ስትጠይቅ ነበር ያቆምነው ቀጥዬን እነሆ……………ከክፍሉ ውስጥ የምትፈልጊው ካለ አውጭ አለችኝ።ለምን? አልኳት ቤቱን ልዘጋው ነው ከዚህ በኋላ እኔና አንቺ አብረን መኖር አንችልም አለችኝ እኔም ምንም እንደማልፈልግ ነገርኳት በወቅቱ እኔ በጣም ደነገጥኩ ታላቅ እህቴ ደግሞ በቦታው አልነበረችም ስትመጣ ቤታችን መቆለፉንና መባረራችንን ስነግራት ጌታ ይመስገን አለች ኝ ነገሩ ያልገባት መስሎኝ ከቤት ተባረርን ነው የም ልሽ ብላት ገብቶኛል ጌታ መኖሪያ ያዘጋጅልናል አለ ችኝ እኔም እሷን ሳይ በረታሁ በዚህ ሙልኩ ቤታችን ተቆልፎ ተባረርን ሌሎቹ የኔ ታናናሾች ስለነበሩ ብዙ ትኩረት አልሰጠ ቻቸውም።ወዴት እንደምንሄድ ምን ማድረግ እንዳለብን  አናውቅም ሥራ የለንም ገንዘብ የለንም በተጨማሪ ከቤት ወጥተን አናውቅም ከሞቀ ቤታችን ወጥተን የስደት ኑሮ ጀመርን ለሶስት ቀን የእህቴ ጓደኛ ቤት አደርን ምናልባት በሽማግሌ እንታረቃለን ብለን አስበን ነበር ነገር ግን እንደቀልድ ወጥተን ነገሩ የምር ሆነ ሰዎች ቢለምኗትም በፍጹም አለች ነገር ግን ለአራት ወር ያህል የቤት ኪራይ እና ቀለብ ሰጠችን ሆኖም ሰዎች ይሄ የባሰ አበላሸሻቸው እንጅ ምኑን ተቀጡ ይልቅ ምንም ነገር አታድርጊላቸው መግቢያ ሲያጡ እና ሲራቡ ያኔ ይቅርታ ይጠይቁሻል ብለው መከሯት ከዚህ የተነሳ ያመናችሁት ኢየሱስ የቤት ኪራይ ይክፈልላቸው የሚበላም ይስጣችሁ ብላ ሁሉን ነገር ከለከለችን በዚህ ጊዜ ነገሩ ቤተክርስቲያን ተሰማና አትፍሩ ቤተክርስቲያን ሁሉን ነገር ታደርጋለች በለው አጽናኑን።የቤት ክራይም ከፈሉልን ቀለብም ሸመቱልን።ጌታ በስደት ውስጥ ብዙ ነገር አስተማረን ይበልጥ በእርሱ መደገፍና መታመን ተማርን እንደፈራነው ሳይሆን በታምራት የስደቱን ዘመንን አሳለፍን።ከሁለት ዓመት የስደት ኑሮ በኋላ በቤታችን ተቀጥራ ሱቅ ውስጥ የምትሰራ አንዲት ሴት ቤተሰቦቿን ለመጠየቅ ወደ ሃገሯ ስለሄደች እናቴ ሌላ ሰው አምና ሱቅ ውስጥ ማስገባት ስለፈራች ብቻ ወደ ቤት ተመልሼ ሱቅ ውስጥ እንድሰራ ተጠየኩ ከስደት ይሻለኛል ብዬ ተመልሼ ገባሁ ነገር ግን እሥር ቤት ሆነብኝ በጥዋት ተነስቼ ሱቅ እከፍታለሁ ብዙ ገቢያ ስለነበረ ሙሉ ቀን ቆሜ ነው የምውለ ቁርስ  ምሣ እራቴን እዚያው ነበር የምበላው የማድረውም።በጣም ተሰቃየሁ ነጋ ጠባ አለቅስ ነበር መጸለይም ምንም ማድረግ አልቻልኩም።በዚህ ሁኔታ ለስድስት ወር ቆየሁ ስድስት ዓመት ነበር የሆነብኝ። የስደት ኑሮዬን ናፈኩኝ ምክንያቱም በስደት ውስጥ የገንዘብ ችግር እንጂ የነፃነት ችግር አልገጠመኝም። ሆኖም ጥቂት እንደቆየው  ጌታ የሥራ በር ከፈተለኝ እና ወደ ድሬዳዋ ሄድኩ።አሁን በደንብ ተመቸኝ በራሴ መኖር ጀመርኩ ጥሩም ደመወዝ አገኝ ነበር። እናቴ በእርግጥ ያመንኩት ኢየሱስ እንዳልተወኝ ስታይ ረገብ አለች።ስለኔም ክፉ ሲያወሩላት ዝም በሉ ማለት ጀመረች ከእናቴም ጋር ያለን ግንኙነት ቀስ በቀስ እየተሻሻለ መጣ እህቶቼም በጋብቻ በትምህርት በተለያየ ምክንያት ሁሉም ከቤት ወጥተው በራሳቸው በኖር ጀመሩ።እናቴም ብቻዋን ቀረች አንድ የእህቴ ልጅ አብራት ትኖር ነበር የእኔና የእናቴ ፍቅር እንደገና እየታደሰ መጣ በቀን በቀን እየደወልኩ*

እጠይቃታለሁ በየሳምንቱ እየሄድኩ እሷጋ አድራለሁ
በዚህ ሁኔታ እያለን እናቴ ያማት ጀመር ፍጹም ጤና
አጣች እዚህጋ ሳልገልጸው የማላልፈው ነገር ሁል ጊዜ
ስለ እናቴ አጥብቄ እጸልይ ነበር ካለማጋነን ሳልጸልይ
ላት ያለፈኝ ቀን የለም ሁል ጊዜ በጌታ ፊት እናቴን
አድንልኝ እያልኩ እጮህ ነበር።ምክንያቱ የነበረችበ
ትን እሥራት አውቅ ስለነበር።አስታውሳለሁ አንድ
ጊዜ እጅግ መዳኗል ከመናፈቄ የተነሳ በጌታ ፊት
በእንባ እንዲህ ብዬ ጸለይኩ ጌታ ሆይ እናቴ ለአንድ
ሣምንት እንኳን እውነተኛ ክርስቲያን ሆና ብትሞት
አይቆጨኝም ለካ ጌታ የልመናዬን ቃል ሰምቷል።
ሁል ጊዜ ወደ ቢሮዬ ስገባ የመጀመሪያ ሥራዬ ስልክ
ወደ እናቴ መደወል ነበር ምናልባት ለሊቱን ሲያመኝ
አደረ ካለችኝ ስልኩን ዘግቼ ወደ እርሷ መሮጥ ነው
እኔ የማድናት ይመስለኝ ነበር።ምን አለፋችሁ እናቴ
ለኔ ጣኦት  ሆናብኝ ነበር ጌታ ደግሞ ይህን አልወደ
ደውም ከዚህ የተነሳ አስታውሳለሁ በአንዲት እህት
በኩል አስደንጋጭ መልእክት መጣልኝ እንዲህ የሚል
ጣኦትሽን ከፊትሽ አነሳለሁ እኔ እናትም አባትም እሆ
ንሻለሁ መልእክቱን እንደሰማሁ የምን ጣኦት ነው ብዬ
እህቴን ጠየኳት ምክንያቱም እኔ የማምልከው እግዚአ
ብሔር ነው እናትሽ ጣኦት ሆናብሻለች አለችኝ በወቅ
ቱ መልክቱ አልተቀበልኩትም።እናቴ የባእድ አምልኮ
ታመልክ ስለነበረ በሕይወቷ ብዙ ውጣ ውረድ ነበረባ
ት በሽታ ዋ ከዚያ የተነሳ  እንጂ የሥጋ በሽታ ወይን
ም በእርጅና ምክንያት የመጣ አልነበረም አስታውሳለ
ሁ ከአንድ  ሁለት ጊዜ ለሞት የሚያደርስ ያህል ታ
ማ ጌታን በፀሎት የሙጥኝ እያልኩ እራርቶልኝ ተፈ
ውሳለች ይህ በእንዲህ እንዳለ በአንድ ወቅት በጠና
ታመመችና ለተሻለ ሕክምና አዲስ አበባ እህቴ ጋ ሄ
ደች እዚያም በሽታው እየጸናባት ሄዶ ሆዱም አበጠ
ይህን በሰማሁ ጊዜ በጣም ደነገጥኩ በጣምም አዘንኩ
ሥራዬንም መስራት አቃተኝ ይህንን ያየ አለቃዬ የዓ
መት  ፈቃዴን ወስጄ ብሄድ የተሻለ እንደሆነ ነገረኝ
እና ተነስቼ ወደ አዲስ አበባ ሄድኩ እናቴ በአንድ
የግል ሆስፒታል ተኝታ እየታከመች አገኘኋት በጣም
ታማ ለች ሆዱም አብጧል ሳያት አለቀስኩ ምክንያቱ
ም ሰው ሆዱ ካበጠ አይተርፍም የሚባል ነገር ስለማ
ውቅ ሆኖም በጌታ ተስፋ አይቆረጥም ከቤተሰቦቼ ጋር
በጣም መጸለይ ጀመርን እህቴ ስለጌታ እየነገረቻት
በየቀኑ ንሰሐ ታስገባት ነበር እሷም ለምንድነው አስሬ
ንሰሐ የምታስገቢኝ ትላት ነበር ለካ ከልቧ አልነበረም
ንሰሐ የምትገባው ጌታም ይህን ስለሚያውቅ በእህቴ
በኩል ደጋግሞ ንሰሐ ያስገባት ነበር።ታድያ በአንድ
ወቅት እኔ አጠገቧ አለሁ ሊጠይቋት የመጡ ዘመድ
በሌላ በኩል ቁጭ ብለ ዋል ድንገት እየደከመች መጣ



(እህት መቅደስና ቤተሰቦቿ)

ችና ተወራጭ  ታ ጥርሷን ግጥም አደረገች አይኖቿን
አፍጥጣ ፀጥ  አለች ትንፋሽ የለም ድምጽ የለም በቃ
ሞተች። ታናሽ እህቴ በሩን ከፍታ ስትባ ተወራጭታ
ፀጥ ስትል አየቻትና ኢ...የ..ሱ..ስ እያለች ጮኸች
ሌሎቹ  በሩ ላይ  ነበሩ እየሮጡ ተከተትለው ገቡ ሞ
ታለች።ሁሉም ማልቀስ ጀመሩ እህቶቼን ሰው የዟቸ
ው ወደ ቤት ሄደ እህቴ ቤት ይለቀስ ጀመር።እኔ ግን
የናቴን ሞት መቀበል አቃተኝ ምክንያቱም በጌታ ፊት
ስለ እናቴ ብዙ አልቅሻለሁ የተስፋ ቃልም ነበረኝ ጌታ
ደግሞ ታማኝ ነው አደራ አይበላም ሰምቶ ይመልሳል
ታድያ  በዚያን ሰዓት አምናለሁ ድፍረቱን ጌታ ነው
የሰጠኝ ሐኪሞቹ ሊከለክሉኝ ቢያስቡም በግድ ገብቼ
በናቴ ሬሣ ላይ አንድ እጄን በደረቷ አንድ እጄን
አንገቷ ላይ አድርጌ እንዲህ አልኩ ......................!

ቀጣዩ. ወደ ገጽ 7 ዞሯል...............................!!

# *የትምህርት ዓምድ*

## *ቅብብሎሽ……*

***ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ለተወሰነ ጊዜ በተከታታይ ይወጣል ዓላማው እውነተኛና አለማቀፋዊቱ የክርስቶስ ቤተ/ክርስትያን አሁን ያለችበትን ሁኔታ እንድታይና ችግሮቿን ለይታ በማውጣት ወንጌልን በተሻለ መልኩ ለቀጣዩ ትውልድ እንዴት ማቀበል እንደምትችል ለማሳየት የታቀደ ነው ዝግጅት ክፍሉ***

*ትውልድ ክረምት ከበጋ እንደማያቋርጥ ጅረት ነው።ሂያጁ ሲያልፍ አዲሱ በራሱ ጊዜ ካለፈው አብራክ ውስጥ ብቅ ይላል።በዚህ ሁኔታ ትውልድ እየተቀባበለ እየተቀያየረ ይጓዛል።ልብ ሲባል ሂያጁ ትውልድ ለመጪው የሚያቀብለው በእጁ የያዘው ዋጋ አለ ሂያጅ ይኽንን ዋጋ እንዴት ለተተኪው ማስጨበጥ እንዳለበት ያስባል።በግልጽም ይሁን በስውር በዚህ ዋጋ በኩል አልፎ በአዲሱ ትውልድ ውስጥ ለመኖር ይፈልጋል።አንዳንዴም ተራውን መጨረሱን ዘንግቶ በአዲሱ ተረኛ ቦታ ገብቶ በግድ ለመሥራት ሲፋጠጥ ይታያል።ሂያጅ ጊዜውን ጨርሶ ለተተኪው ቦታ መልቀቅ እንዳለበት ቢያውቅም ፈጽሞ እንዲረሳ ግን አይፈልግም።ስለዚህ በመጪው አዲስ ትውልድ ውስ ጥ በስውር ለመኖር በመጓጓት ከራሱ ዘመን ወደ መጪው ዘመን ለሚሸጋገር ጥሪት በራሱ ዘመን ይሰራል። ይኽ ብቻ አይደለም፡አዲሱ ተቀባይ ትውልድ የራ ሱን ነገር ከተቀበለው ዋጋ ጋር አጣጥሞ በራሱ ጊዜ በተራው ይሰራል።ከቀደሙት የተቀበለውን እንደገና ሌላ ውበት ይሰጠዋል።ይህ ድንቅ ቅብብሎሽ ይቀጥላል አዲስ ተብዬው በተራው ሂያጅ ሆኖ ይቀየራል እርሱም ከርሱ ለሚቀጥለው ከአብራኩ ለሚወጣው ሌላ ትውልድ የሚያቀብለውን ዋጋ በተራው ይጨብጣል።በዚህ ዓይነት ትውልድ እምነቱን ባህሉን ያለ ጥሪቱን በሙሉ በቅብብሎስሽ እየተፈራረቀ ይጓዛል።*

*የክርስትና ጉዞም እንዲሁ ነው።ዛሬ በእጃችን ያለው ወንጌል ለዚህ የትውልድ ቅብብሎሽ በቂ ምስክር ነው፡ወንጌል ዘመን ተሻግሮ ለእኛም ለተረኞቹ ሲደርስ ስ አልተለወጠም ወይም ከጊዜው ጋር አልተሻሻለም አሰራሩ ግን ልዩ ልዩ ነው።በሂያጁና በአዲሱ ተረካቢ ትውልድ መካከል ያለውን የቅብብሎሽ ሂደት ያሚያናጋውም በአብዛኛው ይህ የአሠራር ልዩነት ነው።አስረካቢው ትውልድ የራሱን ተሞክሮ በመደገፍ የለመደው አሰራር እንዲዘልቅ ለማድረግ መሟገት ይወዳል። አዲሱ ደግሞ በራሱ ተራ መንገድ የሚሄድበትን የራሱን አዲስ ነገር ይፈልጋል ያን ጊዜ የወንጌል ርክክቦሹን ጤነኝነት የሚፈ ታተን ችግር ይከሰታል።*

*በፊላዴልፍያ የምትገኘው የኒው ኮቨናንት ቤተ/ክርስቲያን መሥራችና መጋቢ የሆኑት ቢሾፕ ሚልተን ግራነም ይኽንን ችግር ከራሳቸው የቤተሰብ ተሞክሮ በማመሳሰል በአንድ ሥፍራ የሚከተለውን ተናግረዋል "ለእኔና ለባለቤቴ በየጊዜው ከልጆቻችን የሚቀርብልን የጫማ ግዥ ጥያቄ እየበረከተ በመሄዱ ልጆቼ ከአገልግሎት ውጪ ናቸው የሚሏቸውን ጫማዎች ቀስ ብዬ ማየት ጀመርኩ።በእኔ እይታ ጫማዎቹ ገና ብዙ ሊያገለግሉ የሚችሉ ጥሬ በመሆናቸው ነገሩ ግራ አጋባኝ ቆም ብዬ የራሴን አስተደደግ አሰብኩ።ለቤተሰቦቼ የመጨረሻ ወንድ ልጅ በመሆኔ ታላላቅ ወንድሞቼ ያደርጉት የነበረው ጫማ ሲወርድ ሲዋረድ እየደረሰኝ አዲስ የሚባል ጫማ ሳላይ ማደጌ ትዝ አለኝ።በዚህ መሃል ባለቤቴ የልጆቻችንን የጫማ ግዥ ጥያቄ ተቀብላ ከማስተናገድ የልቅ ቢያንስ የታላቁ ጫማ ለታናሹ ይሁን አይሁን ማረጋገጥ እንደነበረባት አሰብኩ። ሆኖም ይህ የኔ ትውልድ ተሞክሮ ብቻ ነበር።በዚህ መሃል አንድ ሌላ ነገር ወደ አእምሮዬ መጣና ድንገት አንድ ነገር ገባኝ።ችግሩ የጫማው ማለቅ ሳይሆን የልጆቻችን እግር ማደግ ነበር ካሉ በኋላ ይኽን ሁኔታ በምሣሌነት በመውሰድ የሚከተለውን ቁም ነገር ተናገሩ።"ልጆቻችን ባደጉ ቁጥር ባሉበት ጫማ በግድ እንዲቆዩ ለማድረግ ስንሞክር ከጫማው ጥበት የተነሳ*

*መጀመሪያ ማንከሳቸው አይቀርም።ትንሽ ከቆ ዩም ጫማው በእግራቸው አውራ ጣት መበሳቱ አይቀ ርም ከዚያም በላይ ከቆየ ጭራሹኑ ጫማ አውልቆ በ ባዶ እግር መሄድ ይመጣል።በእግዚአብሔር ቤት እንዲሁነው።ተተኪውን አዲስ ትውልድ በእግዝያብሔር ቤት ለማቆየት ትውልዱን የሚመጥን የጌታን ቃልና እውነት የጨበጠ የጊዜውን ሥራ መሥራት ያስፈልጋል።አዲሱ ትውልድ እንዳያነክስ ቆይቶም እግሩ ከእግዚአብሔር ቤት እንዳይወጣ ዛሬ በወንጌል ቅብብሎሽ ዙሪያ እንድንሰራ የሚጠበቅብን ታላቅ ሥራ አለ በማለት በማይረሳ ምሣሌ ሁኔታውን ገልጸውታል።*

*ስለዘመን ፍፃሜ የተነገሩት ትንቢቶች በገሃድ እየተፈጸሙ ባሉበት በዚህ የዘመን መጨረሻ ይህ የወንጌል ቅብብሎሽ ጉዳይ የወንጌል መልእክተኞችን የሚያነጋግር ዋና ጉዳይ ሊሆን ይገባል።ወንጌልን በእጁ የያዘው የአሁኑ ሠራተኛ ትውልድ ለአዲሱ ተረካቢ ትውልድ እንዴት እንደሚያስረክብ ካላወቀበት የሂያጁ ሩጫ ከንቱ መሆኑ አይቀርም።በቅርብ በተደረገው የኦሎምፒክ ውድድር በዱላ ቅብብል ሩጫ ጥሩ ሮጠው ሳለ ለማሸነፍ ያልቻሉትን የአሜሪካን ሯጮች ማስታወስ ይበቃል።ሯጮቹ በየተራቸው ጥሩ ቢሮጡም የሩጫውን ዱላ ሲቀባበሉ ባለመናበብ በፈጠሩት ስህተት የሚገባቸውን የአሸናፊነት ቦታ(የወርቅ ሜዳሊያ ሳያገኙ ቀርተዋል።በእግዚአብሔር ቤትም እንዲሁ ነው።የወንጌል ቅብብሎሹ ጤነኛ እንዲሆን ትውልዱ መተዋወቅ ተያይቶ መቀባበል ይጠበቅበታል፡፡ከላይ የተጠቀሰውን የወንጌል ቅብብሎሽ በአግባቡ ለማስኬድ ዱላውን ተቀባይ አዲሱ ትውልድ ያለበትን ችግር ወይም የሚያልፍበትን ሁኔታ ቀረብ ብሎ ማወቅ ያስፈልጋል።ይኸንን ተረካቢ ትውልድ ለመርዳት አስረካበ ትውልድ ከራሱ አጥር ወጥቶ የዘመኑን ሁኔታ ሊመረምር ይገባል።በዘመኔው ላይ ጣት ከማውጣትና ከመፍረድ ይልቅ በሚራራ ልብ መቅረብ፤ የተረካቢውን ትውልድ ልብ ከፍቶ ማናገር ይገባል።ጆሮው የሚከፈትበትን ልቡ የሚያርፍበትን በሁሉ አቅጣጫ የሚያልፍበትን የውስጡን ነገር አይቶ መድረስ ይቻላል፡፡ እውነት ነው አዲሱ ትውልድ ከዘመኑ ሥልጣኔ ጋር በስውር ተጠቅልሎ የተቀበለው ብዙ ነገር አለው፡፡ ስለዚህም ውስጡ ሳይወድ በግድ በጥርጣሬና በጥያቄ ተሞልቷል።እንዲያውም የሚሰማውን ቀርቶ በገሃድ የሚያየውን ነገር እንኳ ያለጥያቄ መቀበል ተስኖታል፣ እንደቀደመው ትውልድ ትሰማለህ ስማ…ነገሩ እንዲህ ነው…በቃ! ብሎ በቀላሉ መገላገል አይቻልም።አዲሱ ትውልድ ካለበት ጫናና ዙሪያ ገቡን ካካባቢው አደጋና ወጥመድ የተነሳ ለሁሉ ነገር የየራሱ ጥያቄ አለው፡፡ ዘወትር ቁርጥ ያለ መልስ ይፈልጋል ለጥያቄ ውምላሽ አግኝቷል ተብሎ ሲታሰብ እንኳ ከመልሱ ውስጥ ሌላ ጥያቄ መዝዞ ብቅ ይላል።በዚህም ሆነ በዚያ ትውልዱ የራሱ ጩኸት አለው።ይኸን የውስጥ ጩሁቱን የሚያደምጥለት እየተቀባበለ መውጫ ካሳጣው ወጥመድ የሚያላቅቀው ነፃ የሚያወጣው ነገር የፈልጋል።በማስተዋልና በጥበብ የሚጓዝበትን መንገድ የሚያሳየው ፋና ወጊ መሪ ትውልድ ይሻል፡፡የእግዝያብሔር ቃል የጥበብ ቃል ነው።ትውልድ በየተራው ነፃ የወጣበትም ብቸኛ እውነት ነው።ይኸም ትውልድ በዚህና በዚህ መንገድ ብቻ ነፃ ሊወጣ ይገባዋል።ከዝ ያ በኋላ ቅብብሎሹ መስመር ይዞ ይሄዳል! ይኸንን የወንጌል ቅብብሎሽ ሐዋርያው ጳውሎስ በመልእክቱ በተለያየ ሁኔታ ገልጾታል።በእሲያ ስለነበረው ቆይታውና ስለጊዜው የወንጌል ቅብብሎሽ በአጭሩ "የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ ነግሬአችኋለሁና ምንም አላስቀረሁባችሁም" (ሐዋ 20፡27) በማለት በትጋት የተወጣውን ሃላፊነት ለኤፌሶን ሽማግሌዎች አስታውሳቸዋል።ግዴታውን መወጣቱን ብቻ ሳይሆን ተቀባዩ ቹ ያለባቸውን ኃላፊነት ጭምር በአጽንዖት በመግለጽ ለቀጣዩ የወንጌል ሥራ አበረታታቸዋል።እንዲሁም የተወደደውን ጢሞቲዎስን እንዲህ ብሎታል "ከእኔም የሰማኸውን ለሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ" (2ጢሞ 2፡2) ይኸንን ቃል ልብ ስንለው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሶስት*

ተከታታይ ትውልድ አልፎ በማየት ይናገራል የራሱን ትውልድ፤ የጢሞቲዎስን ትውልድ፤ እንዲሁም ከጢሞቲዎስ ትውልድ የሚረከበውን ሌላ ትውልድ። የወንጌል ሸክም ያለበት ሰው እንዲህ ያያል።ዛሬም እግዚአብሔር እንዲህ የሚያይ አገልጋይ ይፈልጋል አዎን!ታማኝ የወንጌል አገልጋዮች አልፈው የሚያዩት ትውልድ አላቸው።ቅብብሎሹን በታማኝነት ለማስኬ ድ ይተጋሉ።የሚሰሩት ላሉበት ትውልድ ብቻ ሳይሆ ን ለሚመጣውም ጭምር በመሆኑ ትውልድ አቋርጠው በሌላ ትውልድ ዘልቀው ለመድረስ ይናፍቃሉ። በውስጣቸው ያለው የወንጌል እሳት አይበርድም፤ ሳያቋርጥ ይነድዳል፤ ሌሎችንም ያሞቃል፤ ቀስ እያለም ካንዱ ወደሌላው ይዛመታል።ይህ የዚህ ትውልድ ዋነኛ ኢላማ ሊሆን ይገባል!

ይቀጥላል.................!!!!

በወንድም ወርቅነህ ተሰፋዬ

ከገጽ 4 የዞረ.... ምስክር

ሰይጣን ስማ የእናቴን ነፍስ ወደ ሲኦል ይዘህ መውረድ አትችልም በኢየሱስ ስም ነፍሷን መልስ እያልኩ በተደጋጋሚ እየተቃወምኩ ጸለይኩ በቦታው የነበሩ ሰዎች ያበድኩ መስሏቸው በጣም አዘኑልኝ ያለቀሱም ነበሩ እኔ ግን በመንፈሴ የምረዳው ነገር ነበር። በዚህ መሐከል ሐኪሞች መጡና አስወጡኝ እኔ ግን በረንዳው ላይ ቆሜ እየተቃወምኩ መጸለዩን ቀጠልኩ ከተወሰነ ደቂቃ በኋላ አንድ ሐኪም ወደ እኔ መጣ አይዞሽ ደህና ናቸው አለኝ ማመን አቃተኝ ይዞኝ ወደ ውስጥ ስገባ ቀና አድርገው ውኃ ሲያጠጧት አየሁ ከደስታዬ የተነሣ ኢየሱስ እያልኩ ስጮህ ጌታን በራይ አየሁት ሰማያዊ ሆኖ በታላቅ ክብርና ግርማ ቤቱን ሞልቶቷል እየተንቀጠቀጥኩ እየሱሴ አንተ እያለህልኝ ይሄ ሁሉ ስጨነቅ አልኩት ቀስ እያለ እየተራመደ ወደ እኔ መጣ እቅፍ አድርጎ ወደ ደረቱ አስጠጋኝ እና አይዞሽ አለኝ እኔ ግን እባክህ እናቴን አድንልኝ አልኩት ከዚያ እናቴ ወደተኛችበት አልጋ ቀስ እያለ ሄደ በራስጌዋ በኩል ቆሞ አልጋዋን እያረገፈ ሲያንጥፍላት እሷም ልክ እንደርሱ ሰማያዊ ሆና እንደልጅነቷ መልኳ ተመልሶ በደስታ ስትዘል አየኋት ይህ ሁሉ ሲሆን በክፍሉ ውስጥ የነበሩት ሐኪሞች የት እንደገቡ አላውቅም የሚታየኝ ኢየሱስ እና እናቴ ብቻ ነበሩ። በዚህ መልኩ እናቴ ከሞት ተመለሰች ያም ሆኖ ከሆስፒታል ግን አልወጣችም ነበር ነገር ግን ፍጹም ሰላም ሆነች የነበራት ጭንቀት ሁሉ ጠፋ ጌታን ከልቧ ተቀበለች በፊት የማትበላቸውን ምግቦች እንጀራን ጨምሮ መብላት ጀመረች በየቀኑ ከኛ ጋር ትጸልይ ጀመር በደንብ ተለወጠች እኔም ቤተሰቦቼም ጌታን ከልቧ እንደተቀበለች ስናይ በጣም ደስ አለን ሆኖም ይህ በሆነ በሳምንቱ አንድ ነገር ተፈጠረ ሌሊት ነው እኔና ሌሎች ሁለት እህቶቼ ነበርን እናታችን ጋ ያደርነው አንደኛዋ እህቴ ጋደም ብላለች ሌላዋም ደግሞ ተማሪ ስለነበረች ፈተና ስላለ ለማጥናት ቁጭ ብላ እያነበበች ነው እኔም ወደ መኝታዬ ከመሄዴ በፊት ለራሴ ባልገባኝ መልኩ ከወትሮው ለየት ባለ መንገድ ለእናቴ መጸለይ ጀመር ኩ ከእግሯ ጀምሬ መላ ሰውነቷን እየደባበስኩ ጌታ ሆይ እናቴን ለዘላለም ለአንተ አደራ አሳልፌ እሰጥሀ ለሁ እያልኩ እጅግ በመንፈስ ሆኜ ደጋግሜ ጸለይኩላ ት ይህ የመንፈስ ቅዱስ አሰራር እንደነበር አስባለሁ እሷም አሜን እያለች ከልቧ ከእኔ ጋር በፀሎት ትተባ በር ነበር እኔም በጣም ደስ ብሎኝ ለመተኛት ጋደም አልኩኝ።በዚህ ጊዜ ሣባ ማጥናት አልቻልኩም ብላ ተነስታ አጠገቧ ቁጭ ብላ ትጸልይ ጀመር።ከተወሰነ ሰዓት በኋላ ስትጠራት አትሰማም ስትደባብሳት ትንፋ ሽ የላትም ጮኸች እኛም ሮጠን ብናያት እናታችን ሞታለች።የሆነ ደስ የሚል ነገር እያየ ፈገግ እንደሚ ል ሰው ሆና ሞታለች ጣር የለም አልተወራጨችም ፈገግ እንዳለች እናቴ ወደ ጌታ ሄደች።ለመዳኗ አንድም ጥርጣሬ በውስጤ የለም ታድያ አንድ ነገር ትዝ አለኝ በአንድ ወቅት ለአንድ ሣምንት እውነተኛ ክርስቲያን ሆና ብትሞት

አይቆጨኝም ያልኩት ለካ ጌታ ይህን የልመናዬን ቃል ሰምቷል።እናቴ ያለ ጣር ያለጭንቀት ፈገግ እንዳለች ወደ ጌታ ሄደች ጌታዬን እንዲህ አልኩት አሸንፌብሃለሁ ክብር ለጌታ ይሁን በዚህ ቃል ጌታ ድንቅ መዝሙር ሰጥቶኛል ለሕትመ ት የበቃው ሲዲ ላይ አለ የታሪክ ባለቤት እርሱ ነው ና ክብሩን ሁሉ እርሱ ይውሰድ አሜን። **መቅደስ ይህንን ምስክርነቷን ከሰጠችን በኋላ ሶስት እህቶቿን አግኝተናቸው አነጋግረናቸው ነበር።**

እውነት ….. እህት መቅደስ ሙሉ ምስክርነቷን ሰጥታናለች፤ ሆኖም እናንተ ደግሞ እናታችሁ ሆስፒ ታል ገብተው ሕይወታቸው እስካለፈበት እስከ መጨ ረሻዋ ቀን ድረስ ያለውን ነገር በድጋሚ ብትመሰክሩ ልን ብለን በየግል ጠይቅናቸው ነበር ሆኖም የሰጡን ምስክርነት ተመሳሳይ ስለሆነ በጋራ አቀናጅተን አቅር በነዋል። በነገራችን ላይ እህት ሣባ እዚሁ አሜሪካ ነዋሪ ስትሆን የራሔወርቅ እና ዮዲት ነዋሪነታቸው በኢትዮጵያ ሲሆን መቅደስ ይህን ምስክርነት በሰጠች በት ወቅት ሊጠይቋት መጥተው ነው ያገኘናቸው። መልካም ግጥምጥሞሽ ነበር።የራሔወርቅ፤ ዮዲት እና ሣባ እንዲህ ሲሉ መስክረዋል… እናታችን ሁለት ጊዜ ነው የሞተችው።በመጀመሪያው በጣም ነበር ያዘነ ነው ምክንያቱ አሟሟቷ በጭንቅ ነበር ደግሞ ጌታን አታውቅም በአፉዋ እሺ ትበል እንጂ ከልቧ አልነበረም በአጋንንት መንፈስ የታሰረች ሰው ስለነበረች ስቃያም ብዙ ነበር።ያ ሁላችንንም እጅግ አስቆጭቶን ነበር በወቅቱ ስትሞት አጠገቧ የነበረችው መቅደስ ነበረች እኛም ክፍሉ ውስጥ አንሁን እንጂ እዚያው ነበርን ጩኸት ስንሰማ ተከታትለን ገባን እናታችን አይኗን አፍጥጣ ጥርሷን ገጥማ ሞታለች ምንም ትንፋሽ የላትም ሐኪሞችም መጥተው።አያት መቅደስ ግን እኔ የናቴን ሞት አልቀበልም ልጸልይላት ፍቀዱልኝ ስትል ሐኪሞቹ ደግሞ በመገረም እያየት ሞታለች ምንድነው የምትጸልይላት ቢሏት እናቴ አልሞተችም መጸለይ እፈልጋለሁ አለቻቸው እነርሱ ግን ከለከሏት ሆኖም ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ሊነጋገሩ ከበሩ ፈቀቅ ሲሉ ዘው ብላ ገብታ ከውስጥ ቆለፈችባቸውና አጋንትን እየተቃወመች መጸለይ ጀመረች እኛ ሁላች ንም እንጮሃለን እራሳችንን መቆጣጠር አቃተን አፉ ፍሰው ወደ ቤት ወሰዱን እዚያ ለቅሶ ተጀመረ የራሔ ወርቅ ስትናገር መቅደስ ያደረገችውን ባለቤቴ ሲሰማ በጣም ተቆጣ ከዚህ በኋላ ማድረግ ያለብንን ማሰብ ነው ብሎ እሬሣውን ወደ ሐረር የሚወስድ መኪና ፍለጋ ሄደ መቅደስ ግን ብዙ ፀልያ በሩ ከፈተችላቸው ሐኪሞቹ ገቡና እርሷን አስወጧት ነገር ግን ፀሎቷን በረንዳ ላይ ሆና ቀጠለች ይህንን ያየና መሞቷን ያረ ጋገጠው ዶክተር አሁንም እናገኘዋለን ባየን ቁጥር እስካሁን ይገረማል ክብሩ ለጌታ ይሁን።ታዲያ ከተወ ሰነ ደቂያ በኋላ አንድ ሐኪም መጥቶ አይዞሽ ደህና ናቸው አላት ማመን የሚያቅት ነገር ነበር።ወደ ቤት ከሄድን ጀምሮ እስከተመለስንበት ድረስ ያለውን የነገሩን እዚያ የነበሩ ቤተሰቦችና ዶክተሩ ናቸው ቤት ተደውሎ አለሞተችም ደህና ናት ተብሎ ተጠራን ለቀ ስተኞቻችንን እቤት ትተን በፍጥነት ተመለስን ስንመ ጣ ቀና ብላ ቁጭ ብላለች።እግዚያብሔር ታላቅ አም ላክ ነው ስሙ ብሩክ ይሁን።ከዚያ በኋላ ለአንድ ሳም ንት እዚያው ሆስፒታል ቆይታ እንደማንኛው ጤነኛ ሰው ያገኘችውን ሁሉ በፊት የማትበላቸውን ምግቦች ሳይቀር በላች።ጌታን ከልቧ ተቀበለች የልጆቼ አምላክ የእኔም አምላክ ነው ኢየሱስ ጌታ ነው እያለች ከልቧ ደስ ብሏት ለአንድ ሣምንት ኖራ እንደገና ሞተች።ይ ሄኛው ሞት ግን የፃድቃን ሞት የሆነላት ልብ በሚያሳ ርፍ መልኩ ወደ ጌታ ሄደች እኛም በሁለተኛው ሞት አላዘንም ምክንያቱም የት እንደምትሄድ እርግጠኞች ነበርን ብለዋል።በመጨረሻ ሁሉም የሚስማሙበት አንድ ነገር ተናገሩ መቅደስ አሉ ለኛ እንደ ሞዴል ነች ክርስትናን ከመናገር ባለፈ ትኖረዋለች ውድ አንባቢያን በሚ ቀጥለው እትም ስለ ትዳር ሕይወቷና ስለ አገልግሎቷ ከባለቤቷ ከወንድም በላይ ጋር የሰጡንን ምስክርነት ይዘን እንቀርባለን።